ክፍል 5 አድልዎ ፤ማሕበረሰባዊ ጥቃትና የሰዎች ዝውውር ንግድ

ሕጉ ማንኛውንም በዘር ፣ በቀለም ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በፖለቲካና ሌላ አመለካከት ወይም በሕብረተሰቡ ውስጥ ባለው ቦታ የሚደረግ አድልዎን ይከለክላል። ይሁን እንጂ መንግሥት እነዚህን ገደቦች በተግባር አላስፈፀመም ነበር።

ሴቶች፣

የቤት ውስጥ ጥቃት ፣ በባሎች የሚፈፀመ፡ ድብደባዎችንና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን ጨምሮ ፣ ሰፊ ማህበረሰባዊ ችግሮች ነበሩ። ሐምሌ 2005 በተደረገው በዓለም ባንክ ጥናት ላይ 88 በመቶ የሚሆኑ የገጠር ሴቶችና 69 በመቶ የሚሆኑ የከተማ ሴቶች ባሎቻቸው ሊመቷቸው መብት አላቸው ብለው ያምኑ እንደነበር ደምድሟል።

ምንም እንኳን ሴቶች ለፖሊስና ለፍርድ ቤት ማመልከት ቢችሉም የማህበረሰቡ ደንቦችና ውሱን የሆነው መሠረተ ልማት ብዙ ሴቶች፤ በተለይም በገጠሩ አካባቢ፤ ወደ ሕግ እንዳይሄዱ አግደዋቸዋል። መንግሥት በተወሰነ ደረጃ አጥፊዎችን ወደ ሕግ አቅርቧል።

በጥቅምት 2005 መንግሥት የሴቶች ጉዳይ ቢሮን ወደ ሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍ አድርጎት ነበር ። ይህ ሚኒስቴር ራሱን የቻለና ተጨማሪ ሠራተኞች ያሉት ነበር ። ሌሎች ሁሉ አስፈላጊ ቢሮዎችን በ2005 ተከፍተው ነበር ። እነሱም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ውስጥ በምክትል ምኒስትር ማዕረግ በተሾመ የሴቶችና የሕፃናት ኮሚሽነር የሚመራውና በእንባ ጠባቂው ቢሮ የሴቶችና የህፃናት ዕንባ ጠባቂ ቢሮ ነበሩ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል ቢያደርገውም በትዳር ውስጥ ስለሚፈፀመው አስገድዶ መድፈር ግን በግልፅ ያስቀመጠው ነገር የለም ። መንግሥት ይህንን አንቀፅ ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ እንዲሆን አላደረገም ነበር ። ለዚህም ምክንያቶቹ

የሕዝቡ በተለይም የሴቶች አለማወቅና የአቅም ማንባታ ስልጠናዎችና ገንዘብ አለመኖር ነበሩ።

የማህበረሰቡ ደምቦች በተለይ በገጠሩ አካባቢ የችግሩ ቁልፍ መንስኤዎች ሆነው ቆይተዋል። የማሕበረሰቡ ደምቦች የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን በመከታተሉና ለሕግ በማቅረቡ ሂደት ላይ እንቅፋት ሆነው ነበር ። ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ሴቶች በሕግ ስለተሰጣቸው መብት አለማወቃቸው ሪፖርት የማይደረጉ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች እንዲበዙ አድርጓል። ታዛቢዎች እንደገመቱት በአዲስ አበባ ብቻ መደ 1000 አካባቢ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች በየዓመቱ የፈፀማሉ ። ነገር ግን የፖሊስ መረጃ እንደሚያመለክተው በዓመት በግምት ወደ 400 ያህል ብቻ ነበር ሪፖርት የሚደረጉት ። ጋዜጦች በቋሚነት የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን በተለይም በሕፃናት ላይ አደጋ ሲደርስ ሪፖርት ያደርጉ ነበር ። የተፈረደባቸውን አስገድዶ ደፋሪዎች ፍርድ ቤቶች ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት በሕጉ በተቀመጠው መሠረት ቀጥተው ነበር ።

ምንም እንኳን ሕገ ወጥ ቢሆንም አማራን፤ ኦሮሚያንና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎችን ጨምሮ፤ ባብዘኛው ያገሪቱ ክልሎች ጠለፋ አንዱ የጋብቻ መንገድ ሆኖ ቀጥሎ ነበር ። መንግሥትም ይህንን ተግባር ለመዋጋት ጥረት አድርጎ ነበር ። ያለፍላጎት የሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነት የአብዛኛው የጥልፊያ ግብቻዎች መገለጫ ሲሆን ብዙ ጊዜም በጠለፋ ወቅት ሴቶች አካላዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ጠለፋዎች በቤተሰቦች፤ በማህበረሰቦችና በጎሣዎች መሃከል ግጭቶችን አስከትለዋል ። በጥልፊያ በሚፈፀም ጋብቻ ጠላፊው ተጠላፊዋ ልታገባው ከተስማማች አይቀጣም፤ ባለስልጣናት ጋብቻውን ካልሰረዙት በቀር። ጠላፊው በጥፋተኝነት

ከተፈረደበት በኋላ እንኳን ባለስልጣናት ተጠቂዋ ልታገባው ከፈቀደች ፍርዱን አያስፈጽሙም ነበር። ያለእድሜ ጋብቻም፣ በሱቲ በአማራና ትግራይ ክልሎች፣ ሌላው ችግር ነበር። በነዚህ ክልሎች ሴት ልጆች 7 ዓመት ሲሞላቸው ለጋብቻ ይገደዳሉ፣ ምንም እንኳን ሕጉ የጋብቻ እድሜ 18 ዓመት ነው ቢልም። ያለእድሜ ጋብቻን ጨምሮ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች የሕብረተሰቡ ግንዛቤ እያደገ እንደነበር የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ።

አብዛኛው የሀገሪቱ ልጃገረዶችና ሴቶች ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል። ልጃገረዶች ገና ሰባት ቀን ሲሆናቸው የሚገረዙ ሲሆን በኮረዳነታቸው ደግሞ ባሰቃቂ ሁኔታ ብልታቸውን ይሰፋሉ። በ2005ቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝብ ብዛትና ጤና ዳሰሳ መሠረት በሴቶች ላይ የሚደረገው ግርዛት ከ80 በመቶ ወደ 74 በመቶ እንዲሁም ሴቶች ለግርዛት የነበራቸው ድጋፍ ከ60 በመቶ ወደ 29 በመቶ ቀንሷል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ማንንም ሴት መግረዝ ከ3 ወር ባላነሰ እስራት ወይም ከ500 ብር ባላነሰ ቅጣት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል። በተመሳሳይም የሴት ልጅን ብልት መስፋት ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል። ይሁን እንጂ ግርዛትን በተመለከተ ምንም አይነት ክስ ፍርድ ቤት አልቀረበም ነበር።

መንግስት ግርዛትን ለማጥፋት የተወሰኑ እርምጃዎችን ወስዷል፣ ይሄ ተግባር እንዳይቀጥልም በሕዝብ ትምህርት ቤቶችና በመገናኛ ብዙሃን በዘመቻ አስተምሯል።

በለጋ ዕድሜ የሚከሰት እርግዝና፤ የእናቲቱ ከባድ የተመጣጠነ ምግብ እጦትና በወሊድ ጊዜ ተገቢውን እንክብካቤ የሚያደርጉ ባለሞያዎች እጦት ለፊስቱላና ለዘላቂ የሽንትና የሰገራ መቆጣጠር ችግር ይዳርጋሉ ። በግምት ወደ 8,700 የሚጠጉ ሴቶች በየዓመቱ በፊስቱላ ችግር ይሰቃያሉ ። ከዚህም በላይ 27,000 ሕክምና ያላገኙ የፊስቱላ ታማሚ ሴቶች በገጠር እንደሚኖሩ ታውቋል ። ለፊስቱላ በሽታ ሕክምና የሚገኘው አዲስ አበባ ባለው ብቸኛው የፊስቱላ ሆስፒታል ነበር ። በዚሁ ሆስፒታል በየአመቱ ከ1000 በላይ የፊስቱላ ቀደ ህክምናዎች ይደረጋሉ ። ለእያንዳንዱ ውጤታማ ቀዶ ጥገና አሥር ሴሎች ወጣት ልጃገረዶች ሊታከሙ ቢገባም ግን ሕክምና አያገኙም ነበር ። በወሊድ ጊዜ የሚከሰት ሞት መጠን በጣም ከፍተኛ ነበር ። ይህም በከፊል ለነፍሰጡር ሴቶች የሚከለከሉ ምግቦች በመኖራቸው፤ በድህነት፤ ካለ ዕድሜ ጋብቻና ከግርዘት በተለይም የሴትን ብልት ከመስፋት ጋር የተያያዙ የወሊድ ችግሮች በሚያስከትሉት ችግር ነበር የሚከሰተው ።

እድሜያቸው ከ18 በላይ ለሆኑ ሰዎች ሴትኛ አዳሪነት ሕጋዊ የነበረ ሲሆን የሴተኛ አዳሪ ድለላና በሴተኛ አዳሪነት ከሚገኝ ገቢ ትርፍ ማካበት በሕግ የተከለከሉ ነበሩ። በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ ሰዎች በተደጋጋሚ ድህነት ወደዚህ ዓይነት ሥራ እንደስገባቸው ሪፖርት ያደርጉ ነበር ።

የህግ ባለሞያ ቤቶች ማህበርና አለማቀፍ የስደተኞች ድርጅት (አይ ኦ ኤም)ብዙ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በኢንዱስትሪዎችና በግለሰብ ቤቶች ለመሥራት የሚጓዙ ሴቶች እንግልት እንደሚደርስባቸው ሪፖርት አድርገዋል። (ክፍል 5፤ ሕገወጥ ዝውውርን ይመልከቱ)

የፆታ ወከባ ተስፋፍቶ ነበር ። የወንጀለኛ መቅጫው ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ የእስር ቅጣት ቢደነግግም የፆታ ወከባን የተመለከቱ ሕጎች ተፈፃሚ አልነበሩም ። ምንም እንኳን ሕጉ ሁሉም ሰው እኩል ነው ቢልም መንግሥት ይሄን ሕግ በአግባቡ አላስፈፀመም ነበር። ሕጉ የወንድና ሴት ልጆች ሕጋዊ የጋብቻ ዕድሜ 18 እንደሆነ አስቀምጧል ፤ የፍትሐብሔር ሕጉ ከባህላዊ ሃይማኖታዊ ሕጎች በላይ እንዲሆን አድርጓል፤ በትንሹ ለ5 ዓመታት አብረው የኖሩ ያልተጋቡ ግለሰቦች እኩል ንብረት እንዲካፈሉና የቤተሰብ ሽምግልና ጉባዔዎች እንዲቀሩ አድርጓል፤ ፍርድ ቤቶች በፍቺና መለያየት ወቅት የልጆችን ወይም አቅም የሌለውን የቤተሰብ አባል ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ አዟል፤ በሴቶች ላይም ከፍቺ በኋላ ወይም ባሎቻቸው ከሞቱ በኋላ ድጋሚ

ለማግባት ቢፈልጉ ስድስት ወር መቆየት እንዳለባቸው አሏል ። ይሁን እንጂ የክልል ምክር ቤቶች ለየክልላቸው የቤተሰብ ሕግ የማውጣት መብት ነበራቸው ። የአማራ ፤ የትግራይ፤ኦሮሚያ ክልሎችና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የየራሳቸውን የቤተሰብ ሕግ ያላቸው ቢሆንም የክልል ሕጎች ሁልጊዜም በተመሣሣይ መልክ ተፈፃሚ ሆነው አያውቁም ነበር ። በሕገ እንዲህ ያሉ የክልል ደንቦች ያገሪቱን ሕግ መንግሥት ሊፃረሩ አይችሉም ።

በ2005ቱ ምርጫ ወቅት ኢህአዴግ 30 በመቶ ያህሉ የፓርቲው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሴቶች እንደሚሆኑ ተንብዮ ነበር ። በደርዘን የሚቆጠሩ ሴቶች ኢህአዴግን ወክለው ለምርጫ ተወዳድረው ነበር ። 85 በመቶ ያህሉ ያገሪቱ ሕዝብ በሚገኝባቸው የገጠር አካባቢዎች ሴቶች ላይ የሚደርሰው አድልዎ በጣም የከፋ ነበር ። ሕጉም አድሎአዊ አንቀፆች ይዟል። ለምሳሌ ባል የቤቱ ሃላፊና ከአምስት ዓመት በላይ ያሉ ልጆች ብቸኛ ጠባቂ ነው ይላል ። ባለስልጣናት የቤት ውስጥ ጠብን ለፍቺ መንስኤ አድርገው አይወስዱትም ነበር ።

የባሕላዊ ግብቻ በተወሰነ መልኩ ነበር እውቅና የሚሰጠው ጋብቻው ምንም ያህል ዓመታት ቢቆይ፣ ምን ያህል ልጆች ቢወለዱና ቢያድጉ እንዲሁም የጋራ ሃብት ቢኖር ባሕላዊው ግብቻ ሲቋረጥ ሕጉ ለሴቶች የ3 ወር የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነበር የሚፈቅድላቸው ። ባልየው ለቤተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ግዴታ ስላልነበረበት ሴቶችና ሕፃናት አንዳንዴ ለመበተን ይገዳዱ ነበር ። ሕጉ ማንኛውም ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት በባለቤትነት ይዙት የነበረው ተጋቢ የግል ንብረት ነው ይላል። በጋብቻ ወቅት የፈራ ማንኛውም ንብረት ደግሞ የጋራ ንብረት በመሆኑ በእኩል ይካፈላል። ይሁን እንጂ ሚስት የሟች ባሏን ንብረት የመውረስ መብት የላትም። ጠንከር ባሉ ሕጎች ውስጥ እንኳን አብዛኞቹ የገጠር ኗሪዎች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተራክቧቸው ባሕላዊ ሕጉን መጠቀማቸውን ቀጥለው ነበር ።

መሬት የመንግሥት ነው ። ምንም እንኳን ሴቶች መሬት በሊዝ ማግኘት ቢችሉምና መንግሥት መሬትን ለሴቶችም በእኩል የሚያደርስ ፖሊሲ ቢኖረውም የገጠር ማህበረሰቦች ይህንን ፖሊሲ አልፎ አልፎ ነበር የሚያስፈፅሙት ። በሁሉም ክልሎች ማለት ይቻላል ሴቶች በጋብቻ ካልሆነ በቀር መሬት አያገኙም ነበር ። በተግባርም ባል ሲሞት ባብዛኛው ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ከሟች ሚስት ላይ መሬቱን ይወስዱ ነበር ። በከተሞች ለሴቶች ከወንዶች ያነሰ የሥራ ዕድል ከመኖሩም በላይ ያሉትም ሥራዎች ለአንድ ዓይነት ሥራ እኩል የሚከፍሉ አልነበሩም ።

ልጆች

መንግሥት ባለም አቀፍና አገር በቀል መያዶች በሕፃናት ማህበራዊ፣ ጤናና ሕጋዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚደረገውን ጥረት ያግዝ ነበር ። ይሁን እንጂ የተሻሻለ የጤና አገልግሎት፣ መሠረታዊ ትምህርት የማቅረብ ወይም ለህፃናት ጥበቃ የማድረግ አቅሙ የተወሰነ ነበር ።

በ2005 31.5 በመቶ የሚሆኑ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ህፅናት ትምህርት ቤት አልገቡም ነበር ። እንደ ፖሊሲ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ክክፍያ ነፃ ነበር ። በተለይም በገጠሩ አካባቢ ያገሪቱን ወጣት ማስተናገድ የሚችሉ ትምህርት ቤቶች በበቂ ሁኔታ አልነበሩም ። ከዚህምበላይ የትምህርት ቤት ዕቃዎች ዋጋ በብዙ ቤተሰቦች አቅም የሚቻል አልነበረም ። በ2005 73.2 በመቶ የሚሆኑ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ወንዶች ልጆችና 63.6 በመቶ የሚሆኑ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሴት ልጆች ትምህርት ቤት ገብተው ነበር፤በአዲስ አበባ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከገጠሩ ሲተያይ በጣም ከፍተኛ ነበር ።

የመንግሥት ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት 22.4 በመቶ ያህሉ ትምህርት ቤት የገቡ ልጆች ሁለተኛ ክፍልም እንኳ ሳይደርሱ ያቋርጡ ነበር ። እንዲሁም 34.9 በመቶ ልጆች ብቻ ስምንተኛ ክፍልን አጠናቀው ነበር ።

በሕህፃናት ላይ የሚደርስ ጥቃት ችግር ነበር ። የአንድ መያድ አባላት በአዲስ አበባ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ 10 የህፃናት ጥበቃ ክፍሎችን የወጣት አጥፊዎችን እና የወጣት ተጠቂዎችን መብት ለመጠበቅ ሲሉ አቋቋመዋል። ጥቂት የፖሊስ አባላት በህፃናት ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች እና ስለወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ አያያዝ ስልጠና ወስደው አጠናቅቀዋል ።

በልጃረገዶች ላይ የሚፈፀሙ ማሕበረሰባዊ ጥቃቶችም ችግር እንደሆኑ ቀጥለው

ነበር ። ግርዘት ባብዛኞቹ ልጃረገዶች ላይ ይፈፀም ነበር ። (ክፍል 5 ፤ሴቶችን ይመልከቱ) እንደ እንጥል መቁረጥ፤ ግማ መንቀል፤ ያለዕድሜ ጋብቻ፤ጠለፋና ምግብና ሥራ ክልከላ ያሉ ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም ነበሩ ።

በአፋር ክልል ውስጥ ወንዶች ዕድሜያቸው ያልደረሰ ሴቶችን ማግባታቸውን ቀጥለው ነበር። የሚዲያ ዘገባዎች ደግሞ ይሄ ተግባር በሰፊው መተቸቱንና በመጥፎ ሁኔታ እንደሚታይ ያስረዳሉ ። እንደ የክምባታ ሴቶች ራስ አገዝ ማዕከልና የትግራይ ሴቶች ማህበር ያሉ መያዶች በችግሮቹ ላይ ሕብረተሰቡ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ በየአካባቢያቸው ያሉ የህብረተሰብ አባላት በጎጂ ልማዳዊ ተግባሮችና ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለውጠው ነበር ። ባመቱ ውስጥ የአማራና የትግራይ ክልላዊ መንግሥታት ያለ ዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ ልጃረገዶችን የሚያስታምሩባቸው ኘሮግራሞች ዘርግተዋል።

እንደ አለም አቀፍ መያዶች ዘገባ የህፃናት በሴተኛ አዳሪነት እያዳገ የመጣ ችግር ነው ። ከሚበዘበዙት ሰዎች ውስጥ 60 በመቶዎቹ በ16 እና በ25 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ነበሩ። እድሜያቸው ለአቅመሄዋን ያልደረሱ ልጃረገዶች በሆቴል ቤቶች በመጠጥ ቤቶች እንዲሁም በመዝናኛ ከተሞችና በገጠር መኪና ማቆሚያዎች አካባቢ በሴተኛ አዳሪነት ይሰሩ ነበር ። ሥር የሰደደ ድህነት ወደ ከተሞች፣ የሚደረግ ስደት ያለዕድሜ ጋብቻ፣ኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ እንዲሁም ውሱን የትምህርትና የሥራ ዕድሎች ህፃናት ወደዚህ ዓይነት ሕይወት እንዲገቡ እንደገፋፏቸውና ችግሩንም እንዳባሱት ይነገራል ። ጥቂት መያዶች፣ የኢትዮጵያ ጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ፎረም የተባለውንና ወደ ሴትኛ አዳሪነት ተገደው ለገቡ ልጆች መጠለያ የሚሰጠውን ጥበቃ የሚያደርገውንና ወደ ቤታቸው የሚመልሰውን ድርጅት ጨምሮ ህፃናት ተጠቂዎችን ረድተዋል ።

መያዶች የሴተኛ አዳሪ ሴቶች እድሜያቸው ከ11 ዓመት ጀምሮ ያሉ ድሃ ልጃረገዶችን በመመልመል ከኤች አይቪ ኤድስ ወይም ከሌላ በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት ከሚተላለፍ በሽታ ስጋት ነፃ ናቸው እያሉ እንደሚያከራዩአቸው ሪፖርት አድርገው ነበር ። በ2003 የወጣው የፋሚሊ ሄልዝ ኢንተርናሽናል ሪፖርት እንደሚያመለክተው ደንበኞች በግብረ ስጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ናቸው ብለው ያምኑ ስለነበር ትንንሾቹን ልጆች ይመርጡ ነበር ።

አልፎ አልፎ ህፃናትን ካገር ውጪ የሚያዘዋውሩ ሰዎች እንደነበሩ ሪፖርቶች ነበሩ ። ከደቡብ የተወሰዱ ህፃናት ሕጋዊ ያልሆነ የጉዲፈቻ ሥራ በሚሰሩ ሰዎች ወደ ኬኒያ ተወስደው ለሌላ ሃገር ዜጎች በጉዲፈቻ እንደተሰጡ ያልተረጋገጡ ሪፖርቶች ነበሩ።(ክፍል5፤ማዘዋወርን ይመልከቱ)

የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከባድ ችግር ሆኖ ቆይታል።(ክፍል 6መ ን ይመልከቱ) በመንግሥት ግምት መሠረት የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ቁጥር ከ150,000 እስከ 200,000 ይደርስ ነበር። ከዚህ ውስጥ ከ50,000 እስከ 60,000 የሚጠጉት የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት የሚገኙት በአዲስ አበባ ነበር ። የተባበሩት መንግሥታት ህፃናት መርጃ ድርጅት ባገሪቱውስጥ 600000 የጎዳና ተዳዳሪዎች እንዳሉ ሲገምት ከነዚህም ውስጥ ከ100,000 በላይ የሚሆኑት የሚገኙት በዋና ከተማዋ ነበር ይላል። የተባበሩት መንግሥታት ሕፃናት መርጃ ድርጅት የጎዳና

ተዳዳሪነት ችግር ቤተሰቦች ልጆቻቸውን መርዳት ባለመቻላቸው፣ በወላጆች መታመምና በቤተሰብ ገቢ መቀነስ ምክንያት እንደተባባሰ ያምናል። እነዚህ ህፃናት አንዳንዱም በቡድን አሊያም ብቻቸውን ይለምኑ ነበር ወይም ቀጥተኛ ባለሆነ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ነበር ።(ክፍል 6 መን ይመልከቱ) የመንግሥትና የግል ህፃናት ማሣደጊያዎች (እንለማውታኖች) ሁሉንም የጎዳና ህፃናት ማስተናገድ ያልቻሉ ሲሆን ባብዛኛው ከፍ ከፍ ያሉት ልጆች በትንንሾቹ ላይ ጥቃት ያደርሱባቸው ነበር ። ከባድ የገንዘብ እጦት ስለነበረባቸው ሆስፒታሎችም ሆኑ እንለማውታኖች የተጣሉ ህፃናትን አይቀበሉም ነበር ። አንዳንድ ግለሰቦችም አይናቸውን በማጥፋትና አካለ ጎደሎ በማድረግ ለልመና ይጠቀሙባቸው ነበር ።

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር

ሕጉ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ይከለክላል። ይሁን እንጂ ሰዎችን ከአገር ውጪና በአገር ውስጥ በሕገ ወጥ መንገድ የሚያዘዋውሩ እንደነበሩ የሚገልፁ ሪፖርቶች ነበሩ ። አገሪቱ ለግዳጅ ሥራና ለግብረስጋ ብዝበዛ በሕገ ወጥ መንገድ የሚዘዋወሩ ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት መነሻ ምንጭ ሆና ነበር ። ወጣት ልጃገረዶች ወደ ጅቡቲና ወደ መካከለኛው ምስራቅ በተለይም ወደ ሊባኖስ፤ዱባይ፤ሳኡዲ አረቢያና ባህሬን ለማይፈልጉት የቤት ውስጥ አገልግሎት ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ ይወሰዱ ነበር ። ጥቂት ሴቶች በሊባኖስ በኩል ለሴተኛ አዳሪነት ወደ አውሮፖ በህገ-ወጦች ይወሰዱ ነበር ። ጥቂት ቁጥር ያላቸው ወንዶችም ወደ ሳኡዲአረቢያና የባሕረ ሰላጤው አገራት እውቀት በማይጠይቁ ሥራዎች ለመስማራት በሕገወጦች ተወስደው ነበር ። ህፃናትም ሆኑ አዋቂዎች ባገር ውስጥ በሰው ቤት ለማገልገልና አነስ ባለ መልኩም ለሴተኛ አዳሪነትና እንደሱቅ በደረቴና ሽመና ላሉ የግዳጅ ሥራዎች በሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ከገጠር ወደ ከተማ ይዘዋወራሉ ። መያዶች በየዓመቱ ባለም አቀፍ ደረጃ ከ20,000 እስከ 25,000 የሚደርሱ ሰዎች የሕገ ወጥ ዝውውር ሰለባ እንደሚሆኑ ይገምታሉ ።

አይ ኦ ኤም በ2004 ላይ ሪፖርት እንዳደረገው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በአስደንጋጭ ሁኔታ እያደገ መጥቶ እነደነበር ገልጿል ። አንድ የውጭ መንግሥት በ2003 ላይ የሴቶችንና የሕጻናትን ያገር ውስጥ ህገ-ወጥ ዝውውር በተመለከተ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ችግሩ ሰፊ መሆኑን አረጋግጧል። በጣም በርካታ መልስ ሰጪዎች እንዳረጋገጡት ባብዛኛው ያልተደራጁ ወንጀለኛ ደላሎች ሴቶችና ሕጻናትን ሥራ ይገኛል እያሉ በማማለል ከገጠር ወደ አዲስ አበባ እና ወደሌሎች የከተማ ማዕከሎች ይወስዷቸዋል። ከ459 ምላሽ ሰጪዎች ውስጥ 46 በመቶው ያልተማሩ ሲሆኑ 49 በመቶው ደግሞ ከ8ኛ ክፍል ያልዘለሉ ነበሩ። ባዲሱ፣ ቦታ ሲደርሱ 54 በመቶ የሚሆኑት የሰው ቤት ሠራተኛ ሆነው ሲሰሩ 9 በመቶ ያህሉ የህገወጥ ዝውውር ሰለባ ሴቶችና ህጻናት ግን በመጠጥ ቤቶች ውስጥ ፣ በሴተኛ አዳሪነት ወይም በልመና ስራ ይሰማራሉ።

የግል ተቋማት ካገር ውጪ የስራ ዕድል ስለሚያዘጋጁ ህገወጥ ደላሎች ሴቶችን ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሃገራት ፣ በተለይም ወደ ሊባኖስ ፣ ሳኡዲ አረቢያ ፣ ባህሬይንና ዱባይ፣ በቤት ውስጥና በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥረው እንዲሰሩ ይልካቸው ነበር። እነዚህ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ በጂቡቲ ፣ የመንና ሶሪያ በኩል ነበር የሚሸጋገሩት። አዲስ አበባ በሚገኘው አለምአቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ በኩል ወደጂቡቱ ወይም ደግሞ በሱማሌ በኩል ባለው ብዙም ቁጥጥር በሌለበት ድንበር በኩል ነበር በህገወጥ መንገድ የሚዘዋወሩት። በሊባኖስ የሚገኘው የምርመራና ማቆያ ጣቢያ አዛዥ በጥቅምት 2005 ላይ ሪፖርት እንዳደረጉት አብዛኛዎቹ በህገወጥ መንገድ የገቡ 30,000 ኢትዮጵያዊያት ሴቶች ቤይሩት ውስጥ ይሰሩ ነበር። መንግሥትም ካገር ውጪ ስራ የሚፈልጉ ግለሰቦችን መመዝገቡን ቀጥሎ ነበር።

ህጉ ህጻናትና ሴቶችን በህገወጥ መልኩ በሚያዛውር ሰው ላይ እስከ 20 ዓመት የሚደርስ እስራትና የ10,000 ብር ቅጣት ጥሏል። ምንም እንኳን በቅርቡ ተጠርጣሪ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ስር ቢውሉም ለፍርድ

የቀረቡት በጣም ጥቂቶቹ ነበሩ። በቁጥጥር ስር የዋሉ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ባብዛኛው ያለክስ ይለቀቁ ነበር። ይሁን እንጂ በሐምሌ ወር አንድ ሕገወጥ አዘዋዋሪ ተፈርዶበት በ13 ዓመት እስራትና በ5,000 ብር ተቀጥቷል። የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት በሕገወጥ ዝውውር ላይ የወጡ ህጎችን የማስፈፀም ግዴታ ነበረበት። ይሁን እንጂ እነዚህ ተቋማት ባጠቃላይ ውጤታማ አልነበሩም። መንግሥት የዓለም አቀፍ ሕገ ወጥ ዝውውር ምርመራ ጥረቶችን ይደግፍ ነበር። የመንግሥት ባለስልጣናት በሕገወጥ ዝውውር እንደተሳተፉ ፣ የህገወጥ ዝውውርን እንዳቀነባበሩ ወይም እንደደገፉ የሚጠቁሙ ሪፖርቶች አልነበሩም። ይሁን እንጂ የድንበር ጠባቂዎች ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተገቢውን ትኩረት አልሰጡትም ነበር።

መንግሥት በሕገወጥ መልክ ካገር ወጥተው የነበሩ ሰዎች ወዳገራቸው ሲመልሱ በጣም ትንሽ ድጋፍ ያደርግላቸው ነበር። የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ለነዚህ ዓይነት ሰዎች የተወሰነ የሕግ ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። የፌደራል ፖሊስ የቤቶች ጉዳይ ቢሮ ከሚዲያው ጋር በመተባበር ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሚደረግ ስደት ባለው አደጋ ዙሪያ የሕዝቡን ንቃት ለማሣደግ ፕሮግራም ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነበር። ከአይ ኦ ኤም ጋር መወያየትን ጨምሮ ሕገወጥ ዝውውርን ለመግታት በመንግሥት በኩል የተወሰዱ ርምጃዎች ነበሩ ። የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ውጪ ሄደው ለመስራት ያቀዱ ሰዎችን ውል እየተመለከተ አጥጋቢ ያልሆኑትን ሲያፈርስ ነበር። በአየር መንገድ የሚገኙ የኢሚግሬሽን ባለስልጣናትም ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚጓዙ ሰዎችን የሥራ ውል መፈተሻቸውን ቀጥለው ነበር። የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚሄዱ ሠራተኞችን የሚያሰቀጥሩ ድርጅቶችን በመቆጣጠሩ ረገድ ብዙም አልተሳካለትም ነበር። አንዳንድ ህገወጥ ስራ አስቀጣሪ ድርጅቶች ከመንግሠት ዕይታ አምልጠው ይንቀሳቀሱ ነበር። በቤይሩትና በዱባይ የሚገኙት ያገሪቱ ቆንፅላ ፅህፈት ቤቶች ወደ ሊባኖስና ወደ ዱባይ በህገወጥ ሁኔታ የተወሰዱ ሴቶችን ማገዛቸውን ቀጥለው ነበር።

ባመቱ አይ ኦ ኤም ለዳኞች ፣ ለአቃቢያነ ህግ ፣ እንዲሁም ለፖሊስ መኮንኖች የህገወጥ ዝውውርን ወንጀልነት በተመለከተ ስልጠና ሰጥቶ ነበር። እነዚህ ተቋማት ወንጀለኛ ቀጣሪዎችን ወደ ፍርድ ለማቅረብ ያላቸው አቅም የተወሰነ ነበር።

አካል ጉዳተኞች

ህጉ ለአካል ጉዳተኞችም እኩል መብት የሰጠ ቢሆንም መንግሥት እነዚህን መብቶች የሚያስፈፅም ምንም ዓይነት ተቋም አላቋቋመም። አካል ጉዳተኞች አልፎ አልፎ በስራ ላይ ልዩነት እንደሚደረግባቸው ሲያማርሩ ነበር። መንግሥት በየህንጻው አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ መወጣጫ የለውም ወይም ለነሱ የሚሆን አገልግሎት አያቀርብም ነበር። ምንም እንኳን ህጉ የአካልና የአእምሮ ጉድለት ላለባቸው ሰዎች መልሶ ማቋቋሚያ ዕርዳታ ቢያዝም መንግሥት ለዚህ አገልግሎት የመደበው ጥቂት ገንዘብ ነበረ።

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበር በተገኘው መረጃ መሠረት ወደ ሰባት ሚሊዮን የሚጠጉ አካል ጉዳተኞች ነበሩ። የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው ሰዎች በግምት 800,000 ያህል ቢሆኑም ባገሪቱ አንድ የአእምሮ ሆስፒታል ብቻ ሲኖር የአእምሮ ሃኪሞችም በግምት 10 ብቻ ነበሩ። የአካል ጉዳተኞችን መብት የማስከበርና የመጠበቁ ድርሻ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ነበር። ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተገኘ

የገንዘብ ድጋፍ ከዘጠኙ ክልላዊ መንግሥታት በአራቱ አቅማቸው የተወሰነም ቢሆን ባለፉት 3 ዓመታት የአርቲፊሻል እግርና እጅ መስሪያዎች ተቋቁመው ነበር።

አናሳ ብሔረሰቦች ፣ ዘሮችና ጎሣዎች

ባገራቱ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች የነበሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የኦሮሞ ብሄረሰብ የጠቅላላውን ሕዝብ 40 በመቶ ነበረ። ምንም እንኳን ብዙ ቡድኖች ባገሪቱ ፖለቲካዊና ባሕላዊ ኑሮ ሚና ቢኖራቸውም ከሰሜናዊው ደጋማ ክፍል የሚገኙት የአማራና የትግራይ ብሄሮች ዋናውን ሚና ይጫወቱ ነበር። የፌደራሉ ሲስተም በግርድፉ ዋና ዋና ብሄረሰቦችን ተከትሎ ነበር ድንበር ያበጀው። ስለሆነም የክልል መንግሥታት ቀደም ሲል ከነበራቸው የበለጠ በራሳቸው ጉዳይ የመወሰን ስልጣን አግኝተው ነበር። አብዛኛዎቹም የፖሊቲካ ፓርቲዎች ብሄረሰባዊ እንደሆኑ ቆይተዋል።

የጦር ሰራዊቱ ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች ያካተተ ነበር። ይሁን እንጂ የከፍተኛ መኮንኖች ግሩኘ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ይበዙበት ነበር። በግንቦት 2005ቱ ምርጫ ወቅትና እሱን ተከትሎ በተከሰቱት ተቃውሞዎች የትግራይና የጋምቤላ ተወላጅ የሆኑ ወታደሮች ተቃዋሚዎች ጠንካራ በነበሩባቸው እና የአማራ ብሄር ወታደሮች አያስተማምኑባቸውም ባሏቸው በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ተሰማርተው እንደነበረ የሚገልፁ ብዙ ሪፖርቶች ነበሩ።

አልፎ አልፎም ባለሥልጣናት በክልላቸው ያለው ዋና ብሔር አባል ያልሆኑ አስተማሪዎችንና የመንግሥት ሠራተኞች ከስራ እንደሚያባርሩ የሚገልፁ ሪፖርቶች ነበሩ።

ባመቱ ውስጥ የጎሣ ግጭቶች በተለይም በምዕራብ ፣ ደቡብና ምስራቅ ያገሪቱ ክፍሎች አካባቢ መከሰታቸውን ቀጥለው ነበር። አነግና መንግሥት በዛ ያሉ ግጭቶች አድርገው ነበር።በጋምቤላ ፣ ሶማሌና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎችም በጎሣዎች መካከል ግጭቶች ነበሩ።

ባመቱ መስጥ በጎሶች መካከል የተደረጉ ግጭቶች በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ሞት ምክንያት ሆነው ነበር ። በግንቦት መጨረሻና በሰኔ መጀመሪያ ላይ በሶማሌ ክልል ዳሩር በተባለ ለአካባቢ በሁለቱ የጋርሃጂ ጎሣዎች በሆኑት በሃባር ዩኒስና ኢዳጋሌ መካከል በውሃ ማጠራቀሚያ የተነሳ በተፈጠረ ግጭት በትንሹ 39ሰዎች ሲሞቱ 34 ደግሞ ቆስለው ነበር ።

በ2003 መጨረሻ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመንግሥት የተቋቋመው ኢመማ ህጋዊ ሰውነት ወይም የነፃውን ኢመማ ንብረት የመውሰድ መብት እንደሌለው፣ እንዲሁም ባለስልጣናት ከነፃው ኢመማ የወሰዷቸውን ንብረቶች መልሰው ቢሮዎቹ እንዲከፈቱ ወስኖ ነበር። በመንግሥት የሚመራው ኢመማ ይህንን ፍርድ ለጠቅላይ ፍረድ ቤት ይግባኝ በማሉ ጠቅላይ ፍርድቤቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲመለከተው አዞ ነበር። ባመቱ መጨረሻ የጉዳዩ ምርመራ እንደቀጠለ የነበረ ሲሆን መንግሥት ለነፃው ኢመማ እውቅና እንዲሰጠው የተላለፈው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝም ተፈፃሚ አልሆነም ነበር። ከመነሻው ጀምሮ እንደነበረው በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ኢግዜክቲቭ ኮሚቴ ላይ የነበረው የመንግሥት ቁጥጥር እንደቀጠለ ነበር።

ምንም እንኳን ህጉ አሠሪዎች በሰራተኛ ማህበራት አደራጆችና አባላት ላይ ፀረ-ማህበር አድልዎ እንዳያደርጉ ቢደነግግም ማህበራት አሠሪዎች በተደጋጋሚ የማህበር አደራጅ አባላትን ከስራ እንዳባረሩ ሪፖርት አድርገው ነበር። በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች ያለው የሥራ መደራረብ አላግባብ ከስራ የተባረሩ ሠዎች የክስ ሂደት ባብዛኛው አመታት እንዲፈጅ ምክንያት ሆኖ ነበር። እንደ ሰራተኛ ማህበራት መሪዎች ገለፃ በዛ ያሉ ሰራተኞች አላግባብ ከስራ በመባረራቸው የተመሰረቱ የክስ ሂደቶች ከአራትና አምስት አመታት በኋላ እንኳን በእንጥልጥል ላይ ነበሩ። ፀረ-ማህበር አድልዎ በማድረግ ወንጀል የተረጋገጠባቸው አሰሪዎች ያባረሯቸውን ሠራተኞች ወደስራቸው እንዲመልሱ ይደረጉ ነበር፤ እነሱም ባጠቃላይ ይህን ውሳኔ ተግባራዊ ሲያደርጉ ነበር።

ለ. የመደራጀትና ባንድነት የመደራደር መብት

ህጉ ለብዙ ሠራተኞች ባንድነት የመደራደር መብትን አስጠብቆላቸዋል። በተግባርም መንግሥት ዜጐች ይህን መብት በነፃነት እንዲጠቀሙበት ፈቅዷል። የሰራተኛ ጉዳይ ኤክስፐርቶች ከ90 በላይ የሚሆኑ በማህበራት የተደራጁ ሰራተኞች በጋራ በመደራደር ስምምነቶች ላይ እንደደረሱ ገምተው ነበር። ተወካዮቻቸው በመስሪያ ቤት ደረጃ ስለ ደሞዝ ተደራድረው ነበር። በቀጥተኛው የኢንዱስትሪው ዘርፍ ያሉ ማህበራት የሰራተኛ መመሪያዎችን ለማስከበር ጥረት አድርገው ነበር።

ምንም ዓይነት የውጭ ንግድ ማካሄጃ ዞኖች አልነበሩም።

ሕገ መንግሥቱም ሆነ ህጉ ሠራተኞች መብታቸው ሲነካ የስራ ማቆም አድማ እንዲችሉ መብት የሰጣቸው ቢሆንም ህጋዊ ተቃውሞ ማድረግ አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉ የተብራሩ አንቀፆችንም ይዟል። ለምሣሌ የሥራ ማቆም አድማ ከማድረግ ከ30ቀናት በፊት ቀድሞ ማሳወቅ የሚለውን አንቀፅ አይነት። ህጉ ቅሬታ ያላቸው ሠራተኞች አድማውን ከማድረጋቸው በፊት ካሰሪዎቻቸው ጋር እንዲስማሙ ከማዘዙም በላይ በጣም ረጅም የሆነ የስምምነት ሂደትን ያካትታል። እነዚህ አንቀፆች አሠሪ ሠራተኞቹን አላስገባም ለማለት ባለው መብትም ላይ ግን ተፈፃሚ ናቸው። አንድ የተቃውሞ አመፅ እውን እንኒዲሆን ብዙው ሰራተኛ ሊቀበለውና ሊደግፈው ይገባል።

ባመቱ ውስጥ ብዙ ትናንሽ የስራ ማቆም አድማዎች በኮንስትራክሽን ሰራተኞች ተደርገው ነበር። እነዚህ ሰራተኞች ደሞዝ አነሰን እና ያለአግባብ ተቀነስን ብለው ነበር ያመፁት። የተወሰኑት ጥያቄዎቻቸው በድርድር የተፈቱ ሲሆን የቀሩት ሣይፈቱ ቀርተዋል።

ያም ሆነ ይህ ግን በትንሹ ለአሰሪዎችና ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር 10 ቀናት ቀደም ብለው ካሳወቁ፣ ለመስማማት ጥረት ካረጉና ከፍርድ ቤት ፊት ወይም ከሰራተኛ ግንኙነት ቦርድ ፊት ቀርበው ከነበረና የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ ከሰጡ በኋላ የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብት ነበራቸው።

ህጉ በጣም አስፈላጊ በሆኑ አገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ሰራተኞች ማለትም እንደ አየር ትራንስፖርትና የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ሰራተኞች፣ የመብራት ሃይል አቅራቢዎች፣ የነዳጅ ማደያ ሠራተኞች፣ የሆስፒታልና መድሃኒት ቤቶች ሰራተኞች፣ የእሳት አደጋ ሰራተኞች፣ የቴሌኮሙኒኬሽንስ ሰራተኞች፣ እንዲሁም የከተማ ፅዳት ሰራተኞች የስራ ማቆም አድማ እንዳያደርጉ ያግዳል።

ህጉ የሥራ ማቆም ባደረጉ ሠራተኞች ላይ በቀል እንዳይደረግ ያዛል። ይሁን እንጂ የሠራተኛ ማህበራት መሪዎች ብዙ ሠራተኞች መንግሥት ይህን ህግ ያስፈፅማል ብለው እንደማያምኑ ገልፀው ነበር። እነዚሁ መሪዎች ባገሪቱ ባለው ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥርና በፍርድ ቤት የሰራተኞች ጉዳዮች በሚወስዱት ጊዜ ምክንያት ብዙ ሠራተኞች በስራማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች ሰላማዊ ርምጃዎች ላይ መሳተፍ ይፈሩ እንደነበር ሪፖርት አድርገዋል።

የሠራተኛ ህጉ በየክልል መንግሥታቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ እንዲኖርና በመንግሥት ስር ያሉ ድርጅቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማስተላለፍ እንዲችል ይፈቅዳል። ማሻሻያውም ጊዜያዊ የሠራተኛ ጉዳይ ቦርዶች ተመሣሣይ ሥራ እንዲሰሩ በየክልሉ እንዲኖሩ ይፈቅዳል።

በሰኔ መንግሥት የሠራተኛ ህጉን እንደገና ከዚህ በፊት ባልተጠቀሱ በኤች አይቪ/ኤድስ በሽተኞች ላይ አድልዎ ሲደረግና ጉረታ ለሌላቸው ሰዎች የካሣ ክፍያ እንዲሠጣቸው የሚያዝ እንዲሆን አድርጐ አሻሽሎታል።

ሐ. የግዳጅ ጉልበት ብዝበዛ ክልከላ

ሕጉ በህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጨምሮ የግዳጅ ጉልበት ብዝበዛን ቢከለክልም እንዲህ ዓይነት ተግባራት እንደነበሩ ሪፖርቶች ነበሩ። (ክፍል 5 ና 6 *መን ይመልከቱ*) ፍርድ ቤቶችም የግዳጅ ጉልበት ብዝበዛን መቅጣት ይችሉ ነበር።

መ. የህፃናት የጉልበት ብዝበዛን መከልከልና የሠራተኛ ትንሹ ዕድሜ

የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን የሚቃወሙ ህጐች ነበሩ። ይሁን እንጂ መንግሥት እነዚህን ህጐች በተግባር ባግባቡ አላስፈፀማቸውም ነበር። ስለሆነም የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ በከተማም ሆነ በገጠር የጐላ ችግር እንደሆነ ቀጥሎ ነበር። በህጉ መሰረት በደመወዝ ለመቀጠር ትንሹ እድሜ 14 ዓመት ሲሆን ይህ እድሜም ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚጨርሱበት ነው ተብሎ የታሰበ ነው። ይሁን እንጂ ይህ እድሜ ባግባቡ የተከበረ አልነበረም። እድሜያቸው ከ14 እስከ 18 ዓመት የሆኑ ህፃናት አደገኛ ወይም በምሽት የሚሠሩ ሥራዎችን እንዳይሰሩ ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸው ነበር። በህግ በዚህ እድሜ ክልል ያሉ ህፃናት በቀን ከሰባት ሰዓታት በላይ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም። ከዚህም በተጨማሪ ከቀኑ አስር ሰዓት እስከ ጣቱ 12 ሰዓት ምንም አይነት ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፣ በህዝብ በአላት ወይም በእረፍት ቀናት ወይም የትርፍ ሰዓት ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም። መንግሥት አደገኛ የሚለውን ስራ ሲበይን ማንኛውም በፋብሪካ ውስጥ ወይም የሚንቀሳቀሱ ክፍሎች ባሉት ማሽን አካባቢ ወይም ማንኛውም የልጁን ጤና አደጋ ላይ የሚጥል ስራ ነው ይለዋል።

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የህፃናት ሥራ ህግን የማስፈፀም ግዴታ ቢኖርበትም በቂ ገንዘብና ትኩረት አልሰጠውም ነበር። ምንም እንኳን መንግሥት እነዚህን መመሪያዎች በቀጥተኛው የኢንዱስትሪ ሴክተር ውስጥ ለማስፈፀም ጥረት ቢያያደርግም የማህበረሰብ ደህንነት ተቆርቋሪዎች፣ ሲቪክ ድርጅቶች፣ የመንግሥት ባለስልጣናትና አሰሪዎች ባንድነት የሚስማሙት በመላው ሃገሪቱ፣ በተለይም በአርሶአደሩ አካባቢና ቀጥተኛ ባልሆነው ዘርፍ ውስጥ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ በሰፊው እንዳለ ነው። በከተሞች አካባቢ ብዙ ህፃናት ጫማ መጥረግን፣ ሽመናን፣ ውየላን፣ ኩሊነትን፣ ሎተሪንና ሌሎች ጥቃቅን እቃዎች ማዞርንና ከብት ጥበቃን ጨምሮ በብዙ ስራዎች ተሠማርተው ይገኙ ነበር። በገጠር አካባቢዎች ህፃናት የቤተሰቦቻቸውና በሌሎች እርሻ ላይ እንዲሁም እንደ ቤት ሰራተኞች ሰርተዋል።

በ2001 ከአለም አቀፉ ሰራተኞች ድርጅት (አይ ኤል ኦ) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ላይ የተደረገው ጥናት ግኝት እንደሚያስረዳው 40 በመቶ ህፃናት ከስድስት አመታቸው በፊት ስራ ጀምረው ነበር። ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ግኝት መሠረት እድሜያቸው ከ5 እስከ 17 የሆኑ ህፃናት በሳምንት ባማካኝ 32.8 ሰዓታት ይሰሩ ነበር። በግምት 13 በመቶ የሚሆኑት እድሜያቸው በአምስት እና በዘጠኝ መካከል የነበረ ወንድና ሴቶች ህፃናት በሣምንት ከ58 እስከ 74 ሰዓታት ይሰሩ ነበር። በጥናቱ ከተካተቱት ህፃናት ከሁለት ሶስተኛው በላይ ሙሉውን ወይም በከፊል ያገኙትን ገንዘብ ለወላጆቻቸው ወይም ለአሳዳጊዎቻቸው ይሰጡ ነበር። አዝመራ ባነሰ ጊዜ የቤተሰብ ገቢ መቀነስና የህፃናት ትምህርት ማቋረጥ ሁለቱ ለህፃናት ሰራተኞች መበራከት አስተዋጽኦ ያደረጉ ምክንያቶች ነበሩ።

ጉልበታቸው የሚበዘበዝ ህፃናት ስራተኞች አብዛኛውን ጊዜ የጥቃት ሰለባዎች ነበሩ። በ1999 የተሰራ ጥናት በሥራ ካልተሰማሩ ህፃናት *ጋር* ሲነፃፀር *ሠራተኛ* ህፃናት በሁለት እጥፍ የአካልና የህሊና ጥቃቶች ይደርሱባቸው እንደነበር ደምድሟል። በጥናቱ ከተካተቱ ህፃናት መሃከል ሲታይ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት በዋናነት በቤት ሰራተኞች ላይ የደረሰ ጥቃት ነበር።

በመንግሥት ብያኔ መሠረት አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚባሉት ሴትኛ አዳሪነትንና የግዞት ስራን ያካትታሉ። ባመቱ ውስጥ ከኦሮሚያና ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች

በመጡ ልጆች ላይ የተፈፀሙ የግዳጅ ሥራዎች ሪፖርት ተደርገው ነበር፤ ባብዛኛውም በቤት ውስጥ ይሰሩ ነበር። (ክፍል 5 ን ይመልከቱ) የቤተሰብ አባላትም ልጃገረዶችን ለሴትኛ አዳሪነት ይገፋፉ እንደነበር ሪፖርቶች ነበሩ። (ክፍል 5 ን ይመልከቱ)

ሠ. ለሥራ አመቺ ናቸው የሚባሉ ሁኔታዎች

ባገሪቱ አገራዊ የሆነ የደሞዝ ወለል የለም ። ነገር ግን አንዳንድ የመንግሥት ተቋማትና ሕዝባዊ ድርጅቶች የራሳቸው ወለል ነበራቸው ። ከደሞዝተኛው ብዙሃኑ የሆኑት የሕዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞች የወር የደሞዝ ወለል በግምት ወደ 200 ብር ገደማ ነበር፤ በባንክና ኢንሹራንስ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች ዝቅተኛ ደመወዝ 230.00 ብር ነበር። የደመወዝና ሌሎች ክፍያዎች ጥናት ቢሮ ሪፖርት እንዳደረገው እነዚህ ደሞዞች ለሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው በቂ የኑሮ ደረጃን አያስገኙም። ስለሆነም ብዙ በደሞዝ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ለመኖር በትንሹ ሁለት ደሞዘተኛ ሰው እንዲኖራቸው ያስፈልግ ነበርና ብዙ ልጆች ያለግዜአቸው ትምህርት እንዲያቋርጡ አስገድዷቸዋል። ከህዝቡ ውስጥ በጣም ትንሹና በከተሞች አካባቢ ያለው ሕዝብ ነበር በደሞዝ የሚተዳደረው ።

ሕጉ በሳምንት የ48 ሰዓታት ስራና (24ሰዓት የእረፍት ጊዜ ነው)ከፍተኛ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈቅድ የግዳጅና የበዛ የትርፍ ሰዓት ሥራን ይከለክላል። ምንም እንኳን መንግሥት ሕጉን ለማስፈፀም ያደረገው ጥረት ውሱን ቢሆንም በተግባር ብዙ በቀጥተኛው ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች በሳምንት 40 ሰዓት ብቻ ነበር የሚሰሩት ።

መንግሥት ኢንዱስትሪውና የሠራተኛው ማህበራት በሥራ ወቅት ለሚደርሱ የጤና እክሎችና ለጥንቃቄ ደረጃ ለማውጣት ተደራድረው ነበር። ይሁን እንጂ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የቁጥጥር መምሪያ በገንዘብ እጥረት ምክንያት እነዚህን ደረጃዎች ባግባቡ ሊያስፈፅማቸው አልቻለም ነበር። የተብራራና ለየዘርፉ የተዘጋጀ የጤናና ጥንቃቄ መመሪያ አለመኖርም አፈፃፀሙን የተቃና እንዳይሆን አድርገውት ነበር ። ሠራተኞች በቅጥራቸው ላይ ችግር ሳይከተልባቸው ራሳቸውን ከአደገኛ ሁኔታዎች የማግለል መብት ነበራቸው። ነገር ግን ብዙ ሰራተኞች ይህን ቢያደርጉ ሥራቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ ይፈሩ ነበር ።